# ጥናት አንድ 2ኛ ጴጥ 1፡1-11 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ኢየሱስ ክርስቶስን በተለይም በቁ1 ላይ አምላካችንና ደግሞም አዳኛችን በማለት ነው የሚያስተዋውቀው። ጴጥሮስ በዚህ ክፍል ውስጥ የእምነታችንን አገኛኘትና ምንጩን ሲናገር ከእግዚአብሄር የተሰጠን ነገር መሆኑን በግልጽ ይነግረናል። የእግዚአብሄርን ጸጋና ሰላም በሙላት መለማመድ የፈለገ አማኝ ማድረግ የሚኖርበት ነገር፤ እግዚአብሄርንና ጌታ ኢየሱስን ለማወቅ የሚችለውን ሁሉ ማድረግ ይኖርበታል።
2. እግዚአብሄር እንደሰጠን የሚናገራቸው በሁለት የተጠቃለሉት ዋነኛ ነገሮች፤ የመጀመሪያዎቹ ለህይወት የሚያስፈልጉን ነገሮች ሲሆኑ፤ ሁለተኛዎቹ ደግሞ ለእውነተኛ መንፈሳዊነት የሚያስፈልጉን ነገሮች ናቸው። እኔ እንደገባኝ ከሆነ መንፈሳዊ ህይወትን ለመኖር ፍላጎትን፣ መሻትንና ሃይልንም ጭምር የተሰጠን ሲሆን እውነተኛና እግዚአብሄር ደስ የሚሰኝበት አይነት መንፈሳዊነትም እንደተሰጠን እረዳለሁ። ይህ ሁሉ የተገኘው ቁ3 እንደሚናገረው፤ የጠራንን እርሱን በማወቃችን እንደሆነ እናነባለን።
3. ይህ ጴጥሮስ ታላቅና ክቡር ተስፋ በማለት የሚናገረው የአማኝን ከዚህ ምግባረ ብልሹና ክፉ ምኞት ከሞላበት የጥፋት ዓለም አምልጦ ከመለኮታዊ ባህርይ ተካፋይ በመሆን ማለትም የልጁን የኢየሱስ ክርስቶስ መልክ ወደ መምሰል የመለወጥን ተስፋ እየጠቆመን እንደሆነ ቁ4 ይነግረናል። እኔ እንደተረዳሁት ‹‹እነዚህ ነገሮች›› የተባሉት እግዚአብሄር ነገሮችን ሁሉ እንዲሰጠን ያነሳሱትን በቁ3 መጀመሪያ ላይ ያሉትን የገዛ ክብሩና፣ በጎነቱን እንደሚል ነው የምረዳው። ለዚህ ሁሉ በምክንያትነት የተነገረው በቁ4 መሰረት ‹‹ክፉ ምኞት›› ነው።
4. ‹‹በዚህም ምክንያት›› ብሎ የሚናገረው ከላይ በቁ3-4 ላይ እግዚአብሄር ለአማኝ እንደሰጠ የተነገሩ ነገሮችን ተመልክተናል፤ እነዚህም ለህይወትና ለእውነተኛ መንፈሳዊነት የሚያስፈልግ ነገር ሁሉና በሌላ በኩል ደግሞ ከርኩሰት ነጻ ሆኖ ከመለኮት ባህርይ ተካፋይ ለመሆን የመብቃት ተስፋ ሁሉ የተሰጠ በመሆኑ፤ በዚህ ምክንያት ትጋት ማሳየት ይጠበቅብናል ማለት ይመስለኛል። የእግዚአብሄር በቁ1 የምናየውን የሁሉ ነገር መሰረት የሆነውን እምነት ሰጥቶን በቁ3-4 ደግሞ ለህይወትና ለመንፈሳዊነት የሚያስፈልገንን ሁሉ እንደሰጠን ስናይ፤ አማኝ ደግሞ ለእድገቱ አስፈላጊውን ትጋት ሁሉ ማድረግ እንደሚገባው እንመለከታለን።
5. ጴጥሮስ እነዚህ የተዘረዘሩት ባህርያት ተትረፍርፈው በሙላት እንዲኖሩን ነው የሚፈልገው። የእነዚህ ባህርያት በአማኝ ህይወት ተትረፍርፎ መኖር የሚያስከትሏቸው ነገሮች፤ በመጀመሪያ ደረጃ ኢየሱስ ክርስቶስን በማወቅ ዳተኞች ከመሆን ሲጠብቁን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ፍሬ ቢሶች ከመሆንም ይጠብቁናል። ጸጋና ሰላም እንዲበዛልን፣ ለህይወትና ለእውነተኛ መንፈሳዊነት የሚሆነንን ነገር ለመቀበልና ከዳተኛነትና ከፍሬ ቢስነት ለመዳን ሁሉ ኢየሱስን ማወቅ መፍትሄ ሆኖ ነው በዚህ ምንባብ ውስጥ የምናየው።
6. ሐዋርያው በቁ9 ላይ እነዚህ ባህርያት ስለሌሉት ሰዎች የሚናገራቸው ሁለት ነገሮች፤ አንደኛ ይህ ሰው የሩቁን የማያይ እውር ነው፤ ማለትም ከዛሬውና አሁን ከሚታየው ነገር አልፎ ወደፊት እግዚአብሄር ሊያደርግ የሚችለውን ማየት አይችልም፤ ሁለተኛ ደግሞ ‹‹ከቀድሞው ሃጥያቱ መንጻቱንም ረስቷል›› ማለትም መሰረታዊ በህይወቱ የተከናወነውን ነገር እንኳን ረስቷል።
7. በእግዚአብሄር የተጠራና የተመረጠ ሰው በጌታ ለማደግና እርሱን ለማወቅ ሙሉ ትጋትን የሚያሳይ እንጂ፤ እኔ ድኛለሁ ከዚህ በኋላ የምኖረውን እንደፈቀድኩት እኖራለሁ ማለት እንደማይችል እንረዳለን።
8. ይህ ‹‹በሙሉ ትጋት›› የሚለው ሃሳብ በቻልኩት ጊዜ፣ ሲመቸኝ፣ ጊዜ ሲተርፈኝ፣ ስፈልግና በመሳሰሉት ሁኔታዎች ራሳችንን የምናሳንፍበት ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ እንዳበረታን በጸሎት፣ ከወገኖች ጋራ ህብረት በማድረግ፣ ቃሉን በማጥናትና በመሳሰሉት ሁሉ በትጋት የምንከታተለው እንጂ በቸልታ ወይም በተመቸን ሰዓት የምናደርገው ነገር እንዳልሆነ ነው የሚያሳስበን።

# ጥናት ሁለት 2ኛ ጴጥ 1፡12-21 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በነዚህ በተለያዩ ቁጥሮች ላይ ጴጥሮስ የሚናገረው በቁ5-7 ላይ ቅዱሳኑን በትጋት አንዱን በሌላው ላይ እየጨመሩ እለት በእለት እንዲያሳድጓቸው የተናነራቸውን እንደ በጎነት፣ ዕውቀት፣ ራስን መግዛትና… የመሳሰሉትን ነገሮች ማለቱ እንደሆነ እረዳለሁ። ይህንን የሚያሳስባቸው ሰዎች ምናልባትም አስቀድሞም ለሚያውቋቸውና በእምነታቸው ለጸኑ ዓይነት ሰዎች ነው።
2. ከእንደዚህ አይነት አነጋገሮቹ እኔ የምረዳው፤ እነዚህ የዘረዘራቸው ነገሮችን ሳይታክት ሊያሳስብ መሞከሩ ሐዋርያው እነዚህ ነገሮች ለእነዚህ ሰዎች ህይወት ምን ያህል አስፈላጊ መሆናቸውን አጥብቆ እንዳመነበት አያለሁ። ከዚህ ክፍል እንደምረዳው አዎ አለ ብዬ አምናለሁ፤ ይኸውም ነገሩ ለሰዎቹ ህይወት እጅግ በጣም አስፈለጊ ሆኖ ስናገኘው ማለት ነው።
3. ለእርሱ ጉትጎታ ተጨማሪ ምክንያት ሆኖታል ብዬ የምለው በቁ14 ላይ የተናገረው ጌታ የገለጠለት ነገር ነው፣ ይኸውም ምድራዊ ድንኳኑን ቶሎ ጥሎ እንደሚሄድ ስላወቀ ነው። በምድር እንድንሰራው የተሰጠን ማናቸውም አገልግሎት እዚሁ የምንሰራው እንጂ በላይ በሰማይ ልንሰራለት ስለማንችል የተሰጠንን አገልግሎት በትጋት እንድንሰራና እንድናከናውነው ያበረታታናል ብዬ አምናለሁ።
4. በዚህ ሥፍራ ጴጥሮስ የሚናገረው በማቴ 17፡1-9 ላይ የኢየሱስ በክብር ፊቱ የመቀየሩንና ከሰማይ የሰሙትን ድምጽ፣ በአጠቃላይ ከኢየሱስ ጋራ ያሳለፉትን ልምምድ አስመልክቶ ነው። የእነጴጥሮስን ምስክርነት ከሌሎች ሰዎች ምስክርነት የሚለየው በነዚህ ቁጥሮች እንደምንመለከተው እነርሱ ሁኔታውን ሲከናወን በአይኖቻቸው ያዩና በጆሮዎቻቸው የሰሙ ስለሆነ በስሚ ስሚ ያልሆነ ቀጥተኛ መረጃ ስላላቸው ልዩ ነው ማለት ይቻላል።
5. አንደኛው ነገር እግዚአብሄር አብ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ደስ እንደሚሰኝበት የሚነግረን ሲሆን፤ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ እግዚአብሄር አብ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደሚወደው በቁ17 ላይ በግልጽ እንመለከታለን። በዚህ ክፍል አብ ለወልድ ሲሰጥ የምናያቸው ሁለት ነገሮች ክብርና ሞገስ ናቸው።
6. ጴጥሮስ እርግጠኛነቱን የሚናገርለት የትንቢት ቃል በቁ16 ላይ ሊያስረዳ የጀመረውን የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በሃይልና በክብር ስለመመለሱ ነብያት የተናገሩትን ትንቢት ነው።
7. የትንቢቱን ቃል በቁ19 ላይ በጨለማ ስፍራ እንደሚያበራ መብራት አድርጎ ነው የሚያቀርበው። ይህ የትንቢት ቃል ብርሃን የሚሰጠው ሌሊቱ እስኪነጋና የንጋት ኮከብ እስኪበራ ድረስ ነው። ቁ19 ሊለን የፈለገው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መጥቶ ሙሉ እውቀት እስኪኖረን ድረስ የእግዚአብሄር ቃል መመሪያና ብርሃናችን አድርገን በእርሱ መመላለስ እንደሚኖርብን ነው የሚያስረዳን።
8. በነዚህ ቁጥሮች ላይ ጴጥሮስ እንድንረዳ የፈለገው ዋነኛ ነገር የእግዚአብሄር ቃል ምንጩ ሰዎች እንዳልሆኑና፤ እያንዳንዱ ሰውም በፈለገው መንገድ የሚተረጉመው ነገር እንዳልሆነ ነው የሚያስረዳን።
9. እርሱ በሥጋ ከተለያቸው በኋላ እንኳን እነርሱ እንዲያስቡ የሚፈልገው ነገር በቁ15 ላይ ‹‹እነዚህን ነገሮች›› በማለት የሚናገራቸውን አሁንም በቁ5-7 ያሉትን ነገሮች ነው። ከዚህ የምማረው ነገር አገልጋዮች ለመንጋው የሚያስፈልገውን ለመመገብ አስፈላጊውን ጥረትና ትጋት ማድረግ እንደሚኖርባቸውና፤ በሌላ በኩል ደግሞ እያንዳንዱ አማኝም ለመንፈሳዊ እድገቱ የሚፈለገውን ትጋት ማሳየት እንደሚኖርበት እማራለሁ።

# ጥናት ሶስት 2ኛ ጴጥ 2፡1-22 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ህዝብ እያለ የሚናገረው በቁ1፡20-21 ላይ የትንቢቱን ቃል ይሰሙ የነበሩትን የእስራኤል ህዝቦች ማለቱ ነው። በቀድሞው ዘመን ‹‹ሃሰተኛ ነብያት›› በእኛ ዘመን ደግሞ ‹‹ሃሰተኛ መምህራን›› ያለበት ምክንያት ለእኔ እንደገባኝ በዚያን ዘመን ነብያቱ የሚናገሩት ቃል በ2ኛ ጴጥ 1፡20-21 እንዳነበብነው ስህተት የማይጠበቅበት ዓይነት ቃል ሲሆን፤ አሁን ግን ያንን እውነተኛ ቃል የሚያስተምሩን ሰዎች ስለሆኑ በተጣመመና ውሸት ቀላቅለው ሊያቀርቡልን ስለሚችሉ መርምሮ የመቀበልና የመጣል ሃላፊነት የእኛ መሆኑን 1ኛ ተሰ 5፡20 ይናግረናል።
2. እነዚህ ሰዎች የዋጃቸውን ጌታ ይክዳሉ፣ ጥፋት የሚያስከትል የስህተት ትምህርት በስውር ያስገባሉ፣ በራሳቸው ላይ ድንገተኛ ጥፋት ያመጣሉ፣ እየተስገበገቡ በፈጠራ ታሪካቸው ሰዎችን ይበዘብዛሉ። አንደኛው በቁ2 ላይ የምናየው ብዙዎች አስነዋሪ ድርጊቶቻቸውን ይከተላሉ ይለናል፣ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ከዚያው ቀጥሎ በቁ2 ላይ በእነርሱ ምክንያት የእውነት መንገድ እንደሚሰደብም እንመለከታለን።
3. የነዚህ ሰዎች የወደፊት ዕጣ ዕድላቸው ወይም መጨረሻቸው ፍርድና ጥፋት እንደሚሆን ቁ3 ግልጽ አድርጎ አስፍሮልናል።
4. እግዚአብሄር በእነዚህ ዓይነት ሰዎች ላይ ሳይፈርድ እንደማይቀር ለማረጋገጥ ጴጥሮስ የተጠቀመባቸው ሶስቱ ነገሮች፡ 1ኛ) ሃጥያት የሰሩት መላዕክት 2ኛ) በውሃ የጠፋው የቀድሞው ዓለምና 3ኛ) ሰዶምና ገሞራ ናቸው። በነዚህ ሁለት ከተሞች ላይ ስለፈረደበት ምክንያት ሲነግረን ‹‹ሐጥያት ለሚያደርጉ ሁሉ ምሳሌ እንዲሆን ነው›› ብሎ ይናገራል።
5. እግዚአብሄር በተለይ ለፍርድ ጠብቆ እንደሚያቆይ በነዚህ ቁጥሮች ላይ የምናያቸው፤ ቁ10 በርኩስ ምኞት የሥጋ ፍላጎታቸውን የሚከተሉና፣ ሥልጣንን የሚንቁ በማለት ሲጠራቸው፤ በተጨማሪም ቁ12 ላይ በስሜታቸው የሚመሩና ልቦና የሌላቸውን አራዊት አድርጎ ያቀርባቸዋል። በይሁዳ ላይ የምናነበው ሚካኤል ባለብዙ ስልጣንና ሃይል ያለው ሆኖ እያለ ዲያቢሎስ ላይ የስድብን ነገር ለመናገር ሳይደፈሩ በዚህ ክፍል የተነገሩትን ሰዎች አደራረግና አካሄድ ሥህተት በግልጽ የሚያሳይ ሁኔታ መሆኑን እንረዳለን።
6. ዓይናቸው ቅንዝር የተሞላ ነው፣ ጽኑ ያልሆኑትን ነፍሳት ያስታሉ፣ ስስትን የለመደ ልብ አላቸው፣ የተረገሙ ናቸው፣ ቀናውን መንገድ ትተው የበለዓምን መንገድ ተከትለዋል፣ የደረቁ ምንጮች፣ በዓውሎ ነፋስም የሚነዱ ደመናዎች ናቸው። ጴጥሮስ በሃሰተኛ አስተማሪዎቹ ላይ ያተኮረው በህዝቡ መሃል መርዝ የሚነዙ፣ ነፍሳትን የሚያስቱ(ቁ14)፣ ከስህተት አምልጠው የወጡትን ወደበለጠ ስህተት ስለሚመልሱ(ቁ18) ሥራቸውንና ባህርያቸውን ለሰፊው ለማጋለጥ አስቦ እንደሚሆን አስባለሁ።
7. ሰዎችን ለማታለል የሚጠቀሙበት መንገድ ‹‹በሴሰኛ ሥጋዊ ምኞት በማባበል ያታልላሉ›› ብሎ ነው ቁ17 የሚነግረን። ለሰዎች የሚገቡት ተስፋ ‹‹ነጻ ትወጣላችሁ›› የሚል ሲሆን ተስፋቸው ስሜት የማይሰጥበት ምክንያትም እነዚህ ሰዎች ራሳቸው የጥፋት ባሪያ ስለሆኑ፣ ባሪያ ሆኖ ለሌላው ነጻነትን መስጠት ስለማይቻል ነው።
8. ከፈተና የሚያድናቸው በእውነት እርሱን እያመለኩ የሚኖሩትን ሰዎች ሲሆን፤ ለፍርድ ጠብቆየሚያቆያቸው ደግሞ ዐመጻኞች ሰዎች መሆናቸውን ይነግረናል።

በወንድሙ ሃብተወልድ ተዘጋጀ (253) 653-4707 ethiowengel.com

# ጥናት አራት 2ኛ ጴጥ 3፡1-18 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ከዚህ መልእክቱ በፊት ጴጥሮስ የጻፈላቸው አንድ መልዕክት ነበረ። ጸሐፊው ሁለቱንም መልዕክቶቹን የጻፈባቸው ሁለት ምክንያቶች፡ የመጀመሪያው ቅን ልቦናቸውን እንዲያነቃቁ ለማሳሰብ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በቅዱሳን ነብያት የተነገረውን ቃልና በሐዋርያት አማካኝነት የተሰጠውን ትዕዛዝ እንዲያስቡ ነው።
2. በምዕራፍ አንድ መጨረሻ ላይ (ቁ20-21) የእግዚአብሄር እውነተኛ ነብያት እውነተኛውን የትንቢት ቃል የሚያመጡ እንደነበሩ የተናገረ ሲሆን፤ ምዕራፍ ሁለትን ውስጥ ግን ገና ሲጀምር ጀምሮ በዚህ ተቃራኒ የሚሰሩ ሃሰተኞችም ነብያት እንደነበሩ ስላስጠነቀቃቸው፣ በዚህ ክፍልም ውስጥ ‹‹ቅዱሳን ነብያት›› ሲል እውነተኞቹን ከሃሰተኞቹ የሚለይበት መንገድ ነው። ይህንን መረዳት የምንችለው በቁ2 ላይ ‹‹በቅዱሳን ነብያት የተነገረውን›› ሲል ብሉይ ኪዳንን፤ ‹‹በሐዋርያት አማካኝነት...የተሰጠውን›› ሲል ደግሞ አዲስ ኪዳንን ይጠቀልላል።
3. ሰዎቹ እንዲያውቁ የፈለገው አንድ ነገር በመጨረሻው ዘመን የራሳቸውን ክፉ ምኞት የሚከተሉ ዘባቾች እንደሚመጡ ነው። ክርስቶስን እንደ ውሸታምና የሰጠውን ተስፋ እንደማይጠብቅ አድርገው ነው ያቀረቡት። ከፍጥረት መጀመሪያ አንስቶ እስካሁን ድረስ ሁሉም ነገር እንዳለ መኖሩን እነዚህ ሰዎች ላለመምጣቱ እንደ ማረጋገጫ አርገው ነው የቆጠሩት። ክህደታቸውንም ሆነ ብለውና አውቀው የሚያደርጉት ድርጊት እንደሆነ ጴጥሮስ በዚህ ክፍል ውስጥ ይናገራል።
4. እግዚአብሄር ከሰው አስተሳሰብ በተለየ መንገድ እንደሚያስብ የሚናገራቸው፤ ለእርሱ አንድ ቀን እንደ አንድ አመት፣ አንድ አመትም ደግሞ እንደ አንድ ቀን መሆኑን ነው የሚያስረዳቸው። እግዚአብሄር እንደ ሰው በጊዜ የተወሰነ ሳይሆን ጊዜና ሰዓት የማይወስነው የወደደውን ለማድረግ ጊዜ የማያጥረው መሆኑን ሲያስገነዝብ ነው። የጌታ መዘግየት ለጴጥሮስ እንደ ትዕግስት የሚያየው ሲሆን፤ የሚታገሰውም እርሱ የሚያተኩረው ብዙዎች ወደ ደህንነት እንዲመጡ መሆኑን እናያለን።
5. ከሌባ ጋራ ነው እያነጻጸረ የሚናገረው። ሰማያት በታላቅ ድምጽ ያልፋሉ፣ የሰማይ ፍጥረት በእሳት ይጠፋል፣ ምድርና በውስጧ ያለ ሁሉ ነገር ይቃጠላል። ነገሮች ሁሉ ፍጻሜአቸውና መጨረሻቸው እንደዚህ ከሆነ፤ አኗኗራችን ቅድስና የተሞላበትና እውነተኛ መንፈሳዊነት ያለው ህይወት እንድንኖር ነው የሚያበረታታን።
6. እኛ ግን ይላል ጴጥሮስ፣ በተስፋ ቃሉ የተነገረውን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንጠብቃለን በማለት አማኝ ሊኖረው የሚገባውን አመለካከት ያስጨብጠናል። እነዚህን አነጋገሮች ስንመለከት እኛ ክርስትያኖች ህይወታችንን ልንኖር የሚገባን ዘወትር የጌታን ምጻት እየተባበቅን ሊሆን እንደሚገባ እንረዳለን።
7. ጳውሎስ በተሰጠው ጥበብ መጠን የጌታን ምጻት አስመልክቶ ጽሑፎችን እንደጻፈ ሲናገር፣ ጳውሎስ የጻፈው ደግሞ ከአንድ በላይ የሆኑ መልዕክቶችን እንደሆነ እናያለን። በመልዕክቶቹ ውስጥ በቀላሉ ለመረዳት የሚያስቸግሩ ሃሳቦች እንደነበሩም ጠቅሷል። ‹‹እውቀት የጎደላቸውና ጽናት የሌላቸው ሰዎች›› በማለት ይጠራቸዋል። በአመጻኞች ስህተት ተስበው እንዳይወድቁ ነው የሚመክራቸው።
8. በቁ9 እና በቁ15 ላይ እንደምንመለከተው የጌታ ለመዘግየቱ ምክንያት ሆኖ የተነገረው የሰዎች መዳን ስለሆነ፤ አማኝ ምጻቱን ማስቸኮል የሚችልበት መንገድ ብዬ የማምነው፤ ጌታ የሰጠን ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ የማድረስ ተልዕኮ በሚገባ ስንታዘዝና ስናደርገው በዚያ መንገድ የጌታን ምጻት ማፋጠን እንችላለን ብዬ አምናለሁ።